የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ)

Amara Survival for Ethiopia's Unity Organization (ASEUO)

# ከዐኅኢአድ የተሰጠ መግለጫ

ቅጽ ፩ ቁጥር ፳ ሰኞ ታህሳስ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲ዓ.ም

**የትግሬ-ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የወጀውን የጥፋት አዋጅ፣ ሕዝቡ በትግሉ ያከሽፈዋል!**

የትግሬ-ወያኔ፣ በትግራይ ክፍለ-ሀገር የራሱን ትንሽነት ያወጀበትንና በዐድዋ የበላይነት የቋጨውን ስብሰባ ጨርሶ ያወጣው የትንሽነቱ ማረጋገጫ መግለጫ የተጻፈበት ቀለም ሳይደርቅ፣ እንደገና ትንሽነቱን አጉልቶ የሚያሳይ በሕዝባችን ፊት ያወጀበትን የሀገር አቀፍ የጭምብል ስብሰባውን ማጠናቀቁንና በሕዝብ ላይ መጠነ ሠፊ ዕልቂ ለመፈጸም ለ17 ቀን መከርኩበት ያለውን የስብሰባ ማጠቃለያ የጥፋት ማረጋገጫ መግለጫ ይፋ አድርጓል። የትግሬ-ወያኔ የበላይነት ጭንብል የሆነው የአሁኑ የኢሕአዴግ ስብሰባ ውጤት ከመቀሌው የሕወሓት መግለጫ ልዩ የሚያደርገው፣ የትግሬ-ወያኔን መኖር ወይም አለመኖር ሊያረጋግጥ የሚችል የአጥፍቶ መጥፋት የመጨረሻ ዝግጅቱ ማሳያ ሆኖ ሊያሳይ የሚችል መሆኑ ብቻ ነው።

ለትግሬ-ወያኔ በኢትዮጵያ ፖለቲካ የበላይነቱን አስጠብቆ እንዲቀጥል ፍላጎት ያላቸው ጥቂት የማይባሉ አድር ባይ የሆኑና አንዳንድ የተስፋ ደግ ነገርን ለመስማት የሚጓጉ ቅን ኢትዮጵያውያን፣ ወያኔ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ ወደ ኅሊናው እንዲመለስ የኅሊና ጸሎት የተማጸኑ እንዳሉ መገመት ይቻላል። አድርባዮቹ ከጸሎት አልፈው፣ ልቡን ለማማለል የሽግግር ሂደቱ አባል መሆን የሚችልበትን መንገድ እንዳመላከቱት ታዝበናል። በተጓዳኝም የሕዝቡን ትግል በመጥለፍ የነሱንም የሥልጣን ቦታን ለማመቻቸት የሚያስችል «የእከከኝ ልከክልህ› ፖለቲካ መሥመር መከተላቸውንም አንዘነጋም።

እነዚህ ሁለት አመለካከቶች የሳቱት ትልቅ ነገር ቢኖር፣ የወያኔ-ትግሬ ከሥረ-መሠረቱ ቢያጥቡት የማይጠራ ዘረ-ባንዳ መሆኑን አለመረዳታቸው ነው። በአገራችን የተቀጣጠለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ዋናና መሠረታዊ ጥያቄ የባንዳ ልጆች ብቻ ሳይሆን፣ አናሳው ቡድን ሠፊውንና የአርበኞቹን ልጆች በበላይነት ሊገዛ አይገባውም የሚል ነው። ሕዝቡ ያነሳቸው መፍክሮች «የወያኔ የበላይነት ይወገድ!»፣ «አድልዖና ዘረኝነት ይቁሙ!»፣ «አትነጣጥሉን!»፣ ዐማራውና ኦሮሞው ሊነጣጠሉ አይችሉም ወዘተ የሚሉ መሆናቸው ግልጽ ነው። ጥያቄዎቹ፣ አብሮነታችንና አገራዊ አንድነታችን ወደነበሩበት ይመለሱ የሚሉ የማያሻሙና ግልጽ ጥያቄዎች ናቸው። ለእነዚህ ትክክለኛ ሕዝባዊ ጥያቄዎች የወያኔውን ጭምብል ኢሕአዴግ የሰጠው መልስ ፣የችግሮቹ ሁሉ ቋጠሮ የሆነው በልዩነት ላይ የተመሠረተው የፌደላዊ አስተዳደር፣ በአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሕይዎት ውስጥ የትግሬ የበላይነት ሠፍቶና ዳብሮ ይቀጥል፣ ይህን በሚቃወሙት ላይ የመከላከያውና የፀጥታው ኃይል የአፈናና የግድያ ተግባሩ አጠናክሮ እንዲቀጥል የአጥፍቶ መጥፋት ተልዕኮውን እንዲወጣ ቀጭን ትዕዛዝ የሰጠበት ነው። ባንድ ቃል መልሱ፣ ኢሕአዴግ የቆመበት የዘር ሥርዓት ትክክልና የማይነቃነቅ ነው የሚል

ነው። የተፈጠሩት ችግሮችም በሥርዓቱ ፈጣን ዕድገት የተነሳ የተፈጠሩ በመሆኑ፣ ችግሮቹ የሚጠበቁ እና የማይታለፉ የዕድገት ችግሮች ናቸው፤ እነዚህንም ችግሮች እንዳለፉት ሁሉ ታግየ የማሸንፋቸው ናቸው የሚል ነው።

ለትግሬ-ወያኔ ዘረፋ ፣ ሙሰኝነት፣ ግድያ፣ የዘር ምንጠራ፣ የመሬት ቅርምትና የዘር ፍጅት፣ የትግሬ ነገድ የሀገሪቱን ሥልጣንና ሀብት ጠቅልሎ መያዝ የሚባሉት ድርጊቶች የአገሪቱ ችግሮች እንዳልሆኑና በትግሬ-ወያኔ አገዛዝ የተፈጸሙ ወንጀሎች እንዳልሆኑ፣ሆነው ቢገኙም በይቅርታ የሚታለፉ እንደሆኑ በመቁጠር፣ የሕዝቡን መሠረታዊ የለውጥ ጥያቄዎች አጣጥሎታል። በኢሕአዴግ ውስጥም የወያኔ የበላይነት የለም፤ የተዘረጋው የፌደራል ሥርዓት ለዚህ ዓይነቱ የበላይነት ቦታ አይሰጥም በማለት ተጨፈኑ ላሞኛችሁ ሲል ተደምጧል። ይልቁንም ይህ ኢሕአዴግ ተብየው መግለጫ፣ የተከሰቱት ችግሮች ሁሉም፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በመሆናቸው፣ በድርጅቱ ታርመው፣ የትግሬ-ወያኔን በሁሉም ዘርፎች የበላይነት አስጠብቆ በሁሉም ነገሮች እንደቀድሞው እንዲቀጥሉ፣ ለዚህ አሻፈረኝ ያሉ ኃይሎችና ቡድኖች፣ «በሕዝበኛነት፣ እና በመርሕ አልባ ግንኙነት» ስም ተጠልፈው እንዲቀጡ ለማድረግ አልሞ የተነሳ እንደሆነ መግለጫው በግልጽ ያስረዳል።

በርግጥ፣ ከባንዳው ወያኔ መልካም ነገር ይመጣል ብለው ተስፋ አድርገው ከነበሩት የዋሖች አኳያ ሁኖ ለሚመለከተው፣ወያኔ አሁን የወሰደው አቋሙ የመጨረሻ ተስፋቸውን ባሕር ውስጥ የገባ አሞሌ ጨው እንዳደረገው መገመት ይቻላል። እነዚህ ቡድኖች ተስፋቸው በለማ መገርሳና በገዱ አንዳርጋቸው መካከል ተገነባ ብለው ያለሙት ህልም፣ በኢሕአዴግ የውስጠ ጥገና ለውጥ ፍሬ አፍርቶ፣ ሕገ-መንግሥቱም እንዳለ ተጠብቆና የሕወሓት ድርጅታዊ የበላይነት ተነስቶ፣ የሥልጣንና የኢኮኖሚ ተሳትፎም መጠነኛ በር ተከፍቶ፣ ከወያኔ ዘረፋ ከሚታፈስ ሀብት በጥቅጥቅ ወንፊት ውስጥ በሚያልፈው ጥፍጣፊ ተጠቃሚ በመሆን፣ የሕዝቡን አፍ መዝጋትና የተቃውሞውን እንቅስቃሴ መቆጣጠር ይቻላል የሚል ነበር። እውነቱ ያሳየው ግን፣ እነሱ የትግሬ-ወያኔ ጥፍጣፊም ሆነ ፍርፋሪ ለመስጠት ፍጹም ዝግጁ አለመሆኑን ነው። በመግለጫ ስም የወጣው አዋጅ፣ ለወዳጅም ለጠላትም ግልጽ ያደረገው፣የትግሬ-ወያኔ የበላይነት የማይረጋገጥባት ኢትዮጵያ ትበታተን፣ ለ17 ዓመት ታግለን በመጣንበትና ለ26 ዓመታት በሥልጣን ላይ ለመቆየት ባስቻለን ሁሉንም ተቃዋሚ ደፍጥጦ የማለፍ መንገዳችን እንገፋበታለን! ለዚህ አጥፍቶ የመጥፋት ጉዞአችንም የመከላከያውና የፀጥታው ዘርፍ ስለሆነ ለነርሱ አስፈላጊው ሁሉ ይደረግላቸው በማለት ለትግሬ-ወያኔ በሥልጣን ለመቆየት ሕዝቡን በማስቃየት ለፈጸሙት ተግባር ምሥጋውን ችሯል። ይህም የትግሬ-ወያኔ መሠረታዊ ዓለማ የመጣው ትግራይን ገንብቶ ሌሎችን አጥፍቶ ተመልሶ ወደጎሬው ለመሄድ መሆኑን ዓላማውና ተግባሩ በግልጽ አሳይተዋል።

ለዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት፣ የወያኔን መነሻና መዳረሻ ቀድሞ ባወቁ የዐማራ ኢትዮጵያውያን ልጆች የተገነባ ድርጅት በመሆኑ፣ የትግሬ ወያኔ ጭንብል የሆነው ኢሕአዴግ በታሪኩ ይህን ያህል ቀን የፈጀው ስብሰባውና ያወጣው የጦርነት እወጃ የአቋም መግለጫ፣ ከጠበቅነው ውጭ ሆኖ አላገኘነውም ። ያወጀው አዋጅ፣ ማንም በሱ ልክ የተሰፋ ሱሪ ያጠለቀ ዘረኛ እና ጨፍጫፊ ሁሉ፣ በሕዝብ ኃይል ሲገፋ የሚያደርገው የቀቢጸተስፋ እና የአጥፍቶ መጥፋት የመጨረሻ እርምጃ መሆኑን ማንም የፖለቲካ ሀ ሁን ለቆጠረ ቀርቶ፣ እህልና ውኃ አቀላቅሎ ለሚመገብ ሰብአዊ ፍጡር የተሰወረ አይሆንም።

የመግለጫው የጥፋት እርምጃ ያነጣጠረው በደፈናው በኢትዮጵያ ሕዝብ እና ከሁሉም በላይ በአንድነት ወዳድ ኃይሎች ላይ እንደሆነ ግልጽ ነው። የዒላማው ዋና ጉዳይ ግን፣ እነርሱ ለበላይነታቸው ይበጀናል ብለው በዐማራና በኦሮሞ ነገዶች መካከል ገንብተውት የዘለቁትን የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ያከሸፉ ቡድኖች ላይ ያነጣጠረ እንደሆነ መግለጫው፣«ሕዝበኛነት፣ መርሕ አልባ ግንኙነት እና ቡድናዊ ስሜቶች» በማለት ለማጥላላት የተጠቀመባቸው ሀረጎችና ጽንሰ ሀሳቦች ያረጋግጣሉ። ሁለቱ ነገዶች ባለፉት 26 ዓመታት የተሠራባቸውን ሤራ አጢነው፣ በደረሱበት በሐቅ፣ በታሪክ እና በባህል ላይ የተመሠረተ አብሮነትና አንድነት የማይበጠስ፣ የማይለያይ፣ ተበጠስና ተለያይ ቢሉትም የማይሆንና የማይቻል እንደሆነ የተገነዘቡ ግለሰቦችና ቡድኖች የጥፋት ዘመቻው ዒላማዎች ሆነው የተቀጠሩ መሆናቸውን መግለጫው አልደበቀም። የኦሮሞውና የዐማራው አንድነት፣ ለየራሳቸው ነገዶች ኅልውና ቀጣይነትም ሆነ፣ ለኢትዮጵያ አገራዊነት ወሣኝ መሆኑን በመረዳት፣ ወያኔ ገንብቶት የነበረውን የልዩነትና የሀሰት ግንብ ደረማምሰው፣ «የኦሮሞው ደም ደማችን ነው!»፣ «የዐማራው ደም ደማችን ነው!» የሚሉት ድምፆች ከሁለቱም ነገዶች ከፍ ብለው መደምጥ፣ወያኔ በሁለቱ ነገዶች ፍቺ የትግሬን የበላይነት አስፍን አቀጥላለሁ ሲል ላቀደው የከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲው ተቃራኒ ሆኖ በመውጣቱ፣ የትግሬ-ወያኔ ለገነባው ሥርዓት ከሥር መሠረቱ የሚያናጋው ሆኖ ቆመ። ይህን ተከትሎም የዐማራው የጎበዝ አለቆች እንቅስቃሴና በኦሮሞው ቄሮዎች የሚመራው ሕዝባዊ አመጽ በተከታታይ ወርድና ቁመቱን እያሳደገ አዲስ አበባ ዙሪያን መከበብ የትግሬ-ወያኔን ኅልውና ጥያቄ ውስጥ ከተተው ። ይህም በመሆኑ የጥፋት ዒላማው በኦሕዴድና በብአዴን ውስጥ ያሉ የነቁና ኅሊናቸው ወደ ሕዝባዊነት ያዘነበሉ ግለሰቦች ላይ ሊሆን እንደሚችል መግለጫው አልደበቀም።

ሙት መሪያቸውና በእርሱም መንፈስ የሚንቀሳቀሱት የትግሬ-ወያኔ ስብስቦች፣ የሰጣቸውን የሙት ቃል ማስጠንቀቂያ ዘግይተውም ቢሆን ያስታወሱት የዛሬዎቹ የዐድዋ ቡድኖች፣ በሁለቱ ማለትም በዐማራና በኦሮሞ ነገዶች መሀል የነበረ የጥንቱ የአብሮነትና የአንድነት ጋብቻ ከወያኔ ዕውቅናና ፍላጎት ውጭ መታደስ፣ ለትግሬ-ወያኔ አገዛዝና ኅልውና ትልቁ ውድቀት ሆኖ ታያቸው። ይህ መሬት የያዘ፣ ከሕዝቡ ውስጥ የፈለቀ፣ ከማንም የፀረ አንድነት ኃይል ቁጥጥር ውጪ ሆኖ፣ በሕዝቡ ነፃ ፍላጎት ላይ ተመሥርቶ እያደገ የመጣ የዐማራና የኦሮሞ አንድነት ወደ ነበረበት የመመለስ ድምፅ ከአድማስ አድማስ ማስተጋባትና መተሳሰብ፣ በሁለቱ ወንድማማች ነገዶች ልዩነትና ጥላቻ ላይ ኅልውናውን ለመሠረተው ሕወሓት የሙት መርዶ ነጋሪ አድርጎ ቆጠረው። የአዋጁም እምብርትም ይህን አንድነት ዕውን እንዳይሆን ከወዲሁ በዓላማው አራማጆች ላይ እግድ ጥሎ ሕዝቡን ተስፋ ለማስቆረጥ እንደሆነ ማንም ይስተዋል አይባልም።

የእውነተኛ የኢትዮጵያ አንድነት አፍቃሪዎች የድል ተስፋ መሠረቱ ያረፈው፣ በነዚህ ሁለት ነገዶች መሀል እየተገነባ በመሄድ ላይ ያለው የአንድነት መንፈስ ሁሉንም የሀገራችንን ነገዶች በማሰባሰብ የዲሞክራሳዊት ኢትዮጵያን መሠረት ይጥላል ሚል እምነት ነው። የሁለቱን ነገዶች የአንድነት ጅምር ጉዞ እንዳይጠናከር ከወዲሁ ለማጥፋት ወያኔ ያወጀው የጥፋት አዋጅ ዒላማ የእነዚህ ሁለት ነገዶች የአንድነትና የኅብረት እንቅስቃሴ ለመደፍጠጥ መሆን፣ የሁለቱን አንጋፋ ነገዶችን የአንድነት አራማጅ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና ስብስቦችን ይበልጥ በትብብርና በመደጋገፍ ዙሪያ ጠንክረውና ተበራተው እንዲሠሩ አማራጭ የሌለው ተመራጭ የጉዞ አቅጣጫቸው አድርገው እንዲይዙት የሚያደርግ ግፊት ሰጪ ኃይል እንዳደረገው ይታመናል። ከዚህ አንፃር የዐማራና የኦሮሞ ነገዶች ድልና ሽንፈት የሚጋሩት የወል ጽዋቸው ሆኖ ቀርቧል። አንድነታቸውን ቢያጠናክሩ የድሉ ባለቤቶች የሚሆኑ የመሆኑን ያህል፣አንድነታቸውን ቢያጡ በጋራ ሽንፈትን የሚጎነጩ እንደሆነ ባለፉት የትግሬ ወያኔ አገዛዝ ዘመን በዓይናቸው ሥር ያዩት መራራ ሐቅ ነው።

የወደፊት ሀገራችን እጣፈንታ ባያሌው የሚወሰነውና የሚመሠረተው እነሱ በሚያደርጉት የጋራ ትግልና መስዋእትነት መሆኑን ከወዲሁ ሊረዱት የሚገባ ቁም ነገር ነው። «ምስጋና ለትግሬ-ወያኔ ይግባውና» የዐማራና የኦሮሞ መነጣጠል በተናጠል ለነገዶቹ ኅልውና፣ በጥቅል ለኢትዮጵያ አንድነት የቱን ያል ጥፋት እንደሆነ አገራችንና ሕዝባችን የሚገኙበት ነባራዊ ሁኔታ ያሳያል። በሕዝብ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑትን የዐማራና የኦሮሞ ነገዶች፣ወያኔ ሆን ብሎ በፈጠረው ነጣጥሎ የማዳከም ሤራ፣ በነገዱ አባሎች ልጆች ላይ የፈጸመው ግፍና መካራ ባለፉት 26 አገዛዙ ዘመኑ ምን ዓይነት መራራና ዘግናኝ ሁኔታዎች እንደተፈጸሙበት በዓይኑ ተመልክቷል። ነገዶቹ ጥቅማቸውም ሆነ ኅልውናቸው ሊረጋገጥ የሚችለው በአንድነታቸው እንጂ፣ በመነጣጠላቸው እንዳልሆነ ነገዶቹ ያሉበት ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ያሳያሉ። ይህንም በመሆኑ፣ በነገዶቹ ልጆች የተጀመረው የአንድነትና የአብሮነት ሕዝባዊ እንቢተኝነት እንቅስቃሴ የዚህ ነባራዊ ሁኔታ ውጤት መሆኑ ግልጽ ነው።

ከዚህ የወያኔ የአጥፍቶ መጥፋት እወጃ በኋላ እኛ፣ የኢትዮጵያን አንድነት ትንሣኤን የምንመኝ ኃይሎች፣ ወለም ዘለም ሳንል፣ ትግላችንን በነዚህ ሁለት ነገዶች አንድነት ዙሪያ፣ ሌሎችን ነገዶቿን የማሰባሰብ ኃላፊነትን ልንወስድ ግዴታችን ይሆናል። እነዚያ በአድርባይነትም ይሁን በፖለቲካ ተላላነት ከወያኔ ዘንድ የጥገና ለውጥ ይገኛል ብለው ያሰቡ ወገኖች የፖለቲካ እርማቸውን አውጥተው፣ ከአንድነት ኃይሉ ጋር ሊቀላቀሉ ይገባል። በመገንጠል የፖለቲካ መሥመር ውስጥ ለዘመናት ላይ እና ታች የሚሉ ወገኖችም ሚናቸውን የመለያው ጊዜ ዛሬ ነው።

በዚህ የአጥፍቶ መጥፋት አዋጅ፣የትግሬ-ወያኔ የመጨረሻ የፖለቲካ አቋሙን ግልጽ አድርጓል። ኢሕአዴግን እንደገና በአዳዲስ ባንዳዎች ለማጠናከር ቁርጠኛ አቋሙ መሆኑን ሳይደብቅ ነግሮናል። ለጥገና ለውጥ የተነሱትን ያጸዳል። በሕዝቡ ውስጥ ሽብር ለመንዛት መከላከያውንና የፀጥታ ኃይሉን አዟል። በበለጠ ሽብር የአገዛዝ ዕድሜውን ለማራዘም ወስኗል። ማንኛውንም ውሳኔውን ከወታደራዊ የበላይነት አኳያ ስለሚመለከተው፣ የነባሩን የትግሬ-የበላይነት በሚያጠናክር መልኩ የመከላከያውና የፀጥታው ወሳኝና ቁልፍ ቦታዎች በታማኝ ትግሬዎች እንዲያዝ ያደርጋል። በመሆኑም ከዚህ የአጥፍቶ መጥፋት አዋጅ ቀጥሎ የሚኖረው የትግሬ ወያኔ አገዛዝ፣ ድፍን ያለ የወታደራዊ አገዛዝ ይሆናል። የትግሬ ወያኔ ሁሉንም ነገር የሚያሰላው ፣ ሲሠፋ የትግሬን ዘር፣ ሲጠብ ደግሞ የዐድዋውን ቡድን የተናጠል ሕይዎት ለማትረፍ በመሆኑ፣ የሚወስደው የዘር ፍጅት ካለፉት ሁሉ የከፋና አሰቃቂ ይሆናል። ሕዝባችን ይህን ዓይነቱን ፍጅት ለመከላከል ከወዲሁ የመንፈስና የአካል ዝግጅት ማድረግ አለበት። ያለምንም ማመንታት ራሱን ከጥፋት ለመከላከል መሣሪያውን በማንሳት አጥፊው ወያኔ ከማጥፋቱ በፊት፣አጥፊውን ቡድን ማጥፋት አለበት። ከዚህ ላይ «ምሳ ወይም እራት ሊያደርጉት የተዘጋጁትን የወያኔ ጥርቅም ቁርስ ለማድረግ፣ ከምንጊዜውም በላይ በቁርጠኝነትና በጽናት ሊቆም ይገባል። ሕዝቡ ራሱን ከጥፋት ለመከላከል ባይፈልግም፣ እልቂቱ ግን ፣አይቀሬ ነው። የትግሬ-ወያኔ ያወጀው የአጥፍቶ መጥፋት አዋጅ፣ ራስን ተከላክሎ ተዋግቶ ገሎ

መሞት፣ ወይም በባርነት እየኖሩ የማይቀረውን የተፈጥሮ ጥሪ፣ተራ በተራ በዘር በመመንጠር ጣረሞትን አራዝሞ በውርደት ማለፍ ነው።

ምርጫው ግን የእያንዳንዱ ሰው ፍልጎት ቢሆንም፣ ተመራጩ ምርጫ መሆን ያለበት፣ እጅን አጣጥፎ አሰቃቂና አሳፋሪ ሞትን በጠላት እንጅ ከመቀበል፣ ታሪክና ትውልድ በኩራት የሚዘክሩት ለነፃነትና ለማንነት ጥሎ ማለፍ ነው።

የትግሬ-ወያኔ ይህ የጥፋት እወጃ የመጨረሻ ለሥልጣን ዕድሜዬ መራዘም ይበጀኛል ያለው ፍርሃትና ጭንቀት የወለዱት የጣረሞት እወጃ ነው። ይህን እወጃ 36ቱ የትግሬ-ወያኔ ጭንብልና የእጅ ሥራ የሆኑት የሁሉም በአዳራሹ ውስጥ የተቀምጡት የወሰኑት አይደለም። ውሣኔው በሂደቱ ያልተስማሙና ሂደቱን አቋርጠው ከተበተኑ በኋላ፣ለወያኔ ሥልጣን ዕድሜ መራዘም በድርጅቶች መካከል እንደካርታ ጨዋታ «የጆከርን» ሚና በሚጫወተው ኤርትራዊው በረከት ሥምዖን አማካኝነት ተዘጋጅቶ የወያኔ ታማኝ ሰዎች ይሁን ብለው የተቀበሉት የጥፋት አውጃ እንደሆነ ከአካሄዱ የምንረዳው ነው። አዋጁ የአናሳዎቹ የትግሬ-ወያኔዎች አዋጅ በመሆኑ፣ የሚያስጠብቀው የተለመደውን የዐድዋ ትግሬዎችን የበላይነት ነው። የሚያስከትለው እልቂት ግን ሁሉንም ነው።

እነለማና ገዱ ያቀነቀኑት የጥገና የለውጥ ሀሳብ፣ እነርሱንና ቆምንለት ያሉትን ነገድ ኅልውናና የኢትዮጵያ አንድነት ትንሣዔ አብሳሪ የመሆን ዕጣው እንዲሣፋ፣እነዚህ በመግለጫው «ሕዝባዊተኛነትና መርሕ አልባ ግንኙነት» በሚል በጠላትነት የተፈረጁ ግለሰቦችና ቡድኖች፣ ወያኔ የሕዝባዊ እንቅስቃሴው መቀጣጫ እንዲሆኑ የራሱን እርምጃ ከመውሰዱ በፊት፣ ቀድመው ከሕዝቡ ተቀላቅለው የወያኔ ጭንብል የሆነውን ኢሕአዴግ በማፍረስ ዕውነተኛ የሕዝብ ልጅነታቸውን ሊያረጋግጡ ይገባል። እነዚህ ወገኖች ይህን ዓይነቱን እርምጃ ከወሰዱ ደግሞ ሕዝቡና የአንድነት ተቃዋሚው ጎራ ለለውጡ ስፋትና ጥልቀት ሊሰጥ በሚችል መልኩ ከጎናቸው የመቆም ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከወዲሁ በግልጽ ማሳየት ይጠበቅበታል። እንዲህም በማድረግ የውያኔን ባንዳዎች ዕርቃናቸውን በማቆም የሕዝቡ ጥያቄ ተገቢ መልስ እንዲያገኝ ማድረግ መቻል አለበት።

የትግሬ-ወያኔ ብቸኛው ጉልበቱ ጦሩና የኢሕአዴግ ጭንብልነት ነው። ያን ጭንብል ከተገፈፈ የሚቀረው የጦሩ አመራር ብቻ ነው። የጦሩን ምንዝር፣ ወገንህን ተከተል በሚል ጥሪ፣ ከሥሩ መናድ ይቻላል። ለማና ገዱ ይህንን ያደርጋሉ ወይስ እንደ ጭዳ በሬ እየተጎተቱ ይታረዳሉ? የሚለው ጥያቄ፣ መልሱ በነርሱ ነፃ ምርጫ የሚወሰን ነው። የሕዝባችን ትግል ሥርዓቱ በጫነበት ጫና ተንገፍግፎ በነሱ ላይ ተነሳ እንጂ፣ እነሱን ተከትሎ አልተነሳም። ሕዝባዊ እንቅስቃሴው በነሱ ጭዳ መሆንም ሆነ ሌሎች ምክንያቶች፣ ከፍጥነቱ የመዘግየት ሁኔታ ቢገጥመው እንጂ፣ የሥርዓት ለውጥ ሳያመጣ ይቀለበሳል አይባልም ። ለዚህም እያንዳንዱ የአንድነት ኃይል ከያዘነው ትክክለኛ የትግል ፈር ሳይወጣ ወደፊት በጽናት መግፋት የወያኔን የአገዛዝ ዕድሜ ማሳጠር ይጠበቅበታል። የወያኔ የአጥፍቶ መጥፋት የጣረሞት የጥፋት አዋጅ ለትግሉ ጥንካሬ ይሆናል እንጂ፣ ሊያዳክመው ከቶ አይቻለውም።

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ህብርት ከወደቀችበት ትነሳለች!

ውድ እናት ሀገር እትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!